# ሰማያዊ፣ መኢአድ እና አንድነት ሰልፎችን በጋራ ካላደረጉ ወያኔ ነው የሚጠቀመው – ናኦሚ በጋሻው

January 29, 2015 -

ግንቦት  20 ቀን 1983 ፣ አንድ ድምጽ ሰማን። በሬዲዮ። «ብስት የወለደው የኢሕአዴግ ሰራዊት ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ይሄንን ሬዲዮ ጣቢያ ተቆጣጥሮታል" የሚል የአንድ የሕወሃት ወታደር ድምጽ።

ያንን ድምጽ ከሰማን ወደ 24 አመት ሊሆነው ነው። ብሶት የወለደው የሕወሃት ሰራዊት መልሶ ብሶትን እና መከራን በሕዝቡ ላይ እየፈጸመ ነው። ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ይዉላል የተባለው ሬዲዮ ሕዝብን ለማሸበር፣ የሕዝብን ጥያቄ አንስተው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች ላይ የዉሸት ፖሮፖጋንዳ ለመንዛት፣ በሕዝቡ አይሞር ዉስጥ የአገዛዙ ገናናት ብቻ ለመሳል በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ላለፉት አንድ ወራት ብቻ ገዢው ፓርቲ፣ ምርጫ ቦርድን እና ኢቲቪ፣ ፋና የመሳሰሉትን በመጠቀም እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ዘመቻ ነው በአንድነት ፣ መኢአድ እና ሰማያዊ ፓርቲ ላይ ከፍቷል። እነዚህን ድርጅቶች፣ እንደጠላት በመቁጠር፣ ሊያጠፉቸው ቆርጦ የተነሳ ይመስላል።

ታዲያ አንድነት፣ መኢአድ እና ሰማያዊ፣ በዚህ መልኩ የሕዝብ ጠላት፣ መሆኑን በገሃድ ካረጋገጠው ሕወሃት ጥቃት ሲደርስባቸው ፣ ጥቃቱን በጋራ መመከት አይጠበቅባቸዉምን ? የተናጥል ጉዞ አብቅቶ፣ ሰላማዊ ሰልፎችንና ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች በጋራ ማቀናጀት ወቅታዊና ኢትዮጵያዊ ጥያቄ አይደለምን?

የአንድነት ፓርቲ ጥር 17 በጠራው ሰልፍ የመኢአድ እና ሰማያዊ/ትብብሩ አባላትና ደጋፊዎች ከአንድነት ጎን ቆመው ሲቀሰቅሱና ትልቅ ድጋፍ ሲሰጡ እንደነበረ ታዝበናል። ሆኖም የአመራር አባላቱ ዝምታ ግን ብዙዎችን አያነጋገረ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም ከአንድ ወር በፊት ሰማያዊ/ትብብሩ በጠራው ሰልፍ አንድነቶች አልተሳተፉም ነበር።

«አንድነቶች ይህን ሴራ(የምርጫ ቦርድ) በማውገዛቸው ተደብድበዋል፤ ነገር ግን ድበደባው ወደ አደባባይ ከመውጣት አያግደንም እያሉ ነው። ይህ ውሳኔያቸው ያስመሰግናቸዋል" ያለው የኢሳቱ ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም፣ «አንድነቶች አሁን በያዙት አቋም ከቀጠሉና ሌሎች ፓርቲዎችም ከተቀላቀሏቸው ታሪክ ሊሰሩ ይችላሉ። በዚህም ይሁን በዚያ ይህ ስርዓት መወገዱ አይቀርም።» ሲል ሌሎች ድርጅቶችም ለአንድነት አጋርነት እንዲያሳዩ ተማጽኗል።

የኢትዮጵያ ሪቪው ኤዲተር «UDJs thus demonstrated that they are the real deal — genuine leaders of a peaceful struggle. They led from the front, took the brunt of the barbaric attack, bled and suffered broken bones, and came out with stronger determination.» ሲል አንድነቶች የከፈሉትን ዋጋ አድንቆ በፊታችን እሁድና ከዚያም በኋላ በሚደረጉ ሰልፎች ሌሎች ድርጅቶችን እንዲቀላቀሉ ጥሪ አድርጓል። «This coming Sunday, UDJ is preparing for another peaceful protest to speak out against last Sunday's police brutality and demand free and fair elections. This time the other opposition parties must join them» ሲልም፣ ኢትዮጵያን ሪቪው ፣ በዚህ ወቅት ሌሎች ድርጅቶ አብሮ በጋራ ለመቆም ፍቃደኛ እንዲሆኑ አሳስቧል።

ዶር አክሎግ ቢራራ «ሕወሃት "ሕብረ-ብሄር የፖለቲካ ድርጅቶች፤ በተለይ አንድነት፤ መኢአድና ሰማያዊ በሕዝብ በኩል ተሰሚነትና ታማኝነት ስለተቀዳጁ ለገዢው ፓርቲ አስጊ ናቸው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ ይመስላል። ስለሆነም፤ እነዚህን ተቀናቃኞች የመንግሥት ስልጣንና ገንዘብ ተጠቅሞ፤ የሕጋዊ ሽፋን–የምርጫ ቦርድ፤ ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊስ–(the veneer of legality, for example, the political machine of the Election Board) ተጠቅሞ ማዳከም፤ ማግለል፤ ቢቻል ዋጋ ቢስ ማዳረግ የመንግሥት ስራ ሆኗል። ዓላማው እነዚህ ተቀናቃኞች በምርጫው እንዳይሳተፉ ለማድረግ ነው» ሲሉ ሕወሃት በተለይም አንድነት፣ ሰማያዊና መኢአድ ላይ እንዳነጣጠረ ለማሳየት ሞክረዋል።

«ቢያንስ፤ በኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ግዛታዊ አንድነት–አገርን በማዳን፤ በሰብአዊ መብቶች መከበር፤ ሕዝብን ከመገረፍ በማዳን፤ በሕግ የበላይነት፤ ለሕዝብ ታዛዢ የሆነ መንግሥት በመመስረት፤ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ፤ በፀረ-ሙስና፤ በፀረ የመሬት ነጠቃ ወዘተ ለመስማማትና አብሮ ለመስራት ይቻላል። መተባበር ከሌለ በተናጠል የፖለቲካ ጩኸቱ ዋጋ ቢስ ነው፤ የትም አያደርስም። ከአርባ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተቃዋሚው ክፍል የሚጠብቀው መጠላልፍን አይደለም። መተባበርን፤ መተሳሰብን፤ ለጋራ ዓላማዎች መቆምን ወዘተ ነው። "ለመተባበር የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሉም፤ በተናጠል የምንታገለው ለዚህ ነው" የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚያገለግሉት ራሳቸውንና ገዢውን ፓርቲ ነው ለማለት ከምንደፍርበት ጊዜ ደርሰናል" ሲሉ ድርጅቶቹ በጋራ የማይንቀሳቀሱ ከሆነ የሚጠቅሙትና የሚያገለግሉት ወያኔን እንደሆነ አስምረዉበታል።

ለምሳሌ ያህል ከላይ የኢሳቱን አቶ ፋሲል፣ ኢትዮጵያ ሪቪውን እንዲሁም ዶር ክሎግ ቢራራን ጠቀስኩ እንጂ ፣ በሶሻል ሜዲያዉ፣ በየሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ ሕዝቡ እየሰጠ ያለው አስተያየት በተለይም አንድነት፣ መኢአድ እና ሰማያዊ/ትብብሩ አብረው ትግሉን እንዲያቀናጁ ነው። ሰላማዊ ሰልፎችን አንዱ ድርጅት ዛሬ ለብቻው እየጠራ፣ በሳምንቱ ደግሞ ሌላው እየጠራ መቀጠሉ ትክክል አይደለም።

በአንድነቶች ላይ የደረሰው ድብደባ፣ እንዲቀላቀሉ አስቀድሞ ጥሪ ቀርቦላቸውም፣ ከዳር ሆነው የታዘቡት የመኢአድ እና የትብብሩ/ሰማያዊ አመራር አባላት፣ በነጋታው ባወጡት መግለጫ ጠንካራ ወገዛ በአገዛዙ ላይ አሰምተዋል። ትብብሩ/ሰማያዊ «ትብብራችን የስርዓቱን ጨካኝነት እያወቁም ቢሆን በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያቸውን ለማቅረብ በስርዓቱ የማይከበረውን ህገ መንግስታዊ መርህ ተከትለው ሰልፍ ለወጡ ቆራጥ የአንድነት አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች አድናቆቱን መግለጽ ይወዳል፡፡" ያለው ትብብሩ/ሰማያዊ በመግለጫው «መስዋዕትነታችሁ ለነገ ድላችን ስንቅ በመሆኑ ይበልጡን ተጠናክራችሁ በጋራ ትግላችን እንደምናጠናክርም እምነታችን ነው» ሲልም ከአንድነት ጋር በጋራ ትግሉና ለማጠናከር ፍቃደኝነት እንዳለው ገጸዋል። መኢአድም በተመሣይ ሁኔት ጠንካራ የወገዛ መግለጫ ያወጣ ሲሆን ለአንድነት አጋርነቱን በተደጋጋሚ እያሳወቀ ነው።

መግለጫ ማውጣት አንድ ነገር ነው። እንግዲህ የሰማያዊ/ትብብር አመራር አባላት፣ እንዲሁም የመኢአድ፣ ከአንድነት ፓርቲ ጋር ፣ ነገ ወይም በሚቀጥለው ሳምንት ሳይሆን ዛሬ፣ አሁን፣ ቁጭ ብለው በመምከር፣ የፊታችን እሁድ የሚደረጉ ሰለፎችን እንዲያስተባብሩ በአክብሮት እጠይቃለሁ። የፊታችን ሰኞ በደሴ፣ በደብረ ታቦር፣ በባህር ዳር፣ እና በአዲስ አበባ ሰልፎች ለማድረግ የእወቁልን ደብዳቤ ለባለስልጣናት ተልኳል። በደሴ አስተዳደሩ እውቅና የሰጠ በመሆኑ ሰልፉ በርግጥ ይደረጋል። የአዲስ አበባው እነ የሌሎቹም ደግሞ በቅርብ ይታወቃል ላይ ነው።

በመቀጠልም ደግሞ ትብብሩ/ሰማያዊ በየካቲት ግማሽ ላይ በአንድ ቀን በርካታ ሰልፎች በተለያዩ ከተሞች ለመጥራት ሃሳብ አለው። በዚያን ጊዜ አንድነት እና መኢአድ ተቀላልቅለው በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል። ሪስሮሳቸውን ማቀናጀት አለባቸው። ከአሁን በኋላ አንድነት፣ መኢአድ፣ ሰማይዊ እርስ በርስ የሚፎካከሩት ጊዜ አይደለም። አባላቶቻቸው አንድ ላይ ነው በጎንደር አዘዞ ጦር ካምፕ፣ በማእከላዊ፣ በቃሊቲ፣ ቂሊንጦ ....እየታሰቃዩ ያሉት። ለትግሉ ትልቅ መስዋእትነት እየከፈሉ ያሉ እነ የሺዋስ አሰፋ፣ እነ ርዮት አለሙ፣እ ነ ሃብታሙ አያሌው በጋራ ተንቀሳቀሱ እያሉ ነው። ሕዝቡ በጋራ ተንቀሳቀሱ እያለ ነው።

የፖለቲክ ድርጅቶች በዚህ ወሳኝ ወቅት፣ በጋራ ሰለፎችን የማያደረጉ ከሆነ፣ ዶር አክሎግ ቢራራ እንዳሉት እየጠቀሙት ያለው ወያኔን መሆኑን መረዳት አለባቸው። በተናጥል ሰልፍ እንድንወጣ፣ በተናጥል እንድንቀሳቀስ የሚፈልግው ወያኔ ብቻ ነው። በተናጥል በቀላሉ ለመምታት ስለሚቀለው።

የአንድነቱ መሪ አቶ በላይ ፍቃዱና የመኢአዱ መሪ አቶ ማሙሸት አማረ፣ ድርጅቶቹ አብሮ በጋራ መስራት እንዳለባቸው በተደጋጋሚ በአንክሮት ገልጸዋል። መኢአድ ሰማያዊና አንድነት አብረው አለመስራታቸው ትርጉም የለውም ነው ያሉት። በአንጻሩ የሰማያዊ መሪ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት «የተናጥል ትግል ችግር የለውም» የሚል አቋም ነው ያላቸው። እርግጥ ነው ነገሮች ሰላም በሆኑበት ሁኔታ የተናጥል እንቅሳሴ ችግር ላይኖረው ይችላል። ሆኖም አሁን አገራችን ኢመርጀንሲ ላይ ነው ያለችው። ዶር አክሎግ እንዳሉት የተናጥል ጉዞ በአሁኑ ወቅት፣ የሚጠቅመው ወያኔንን ብቻ ነው። የሰማያዊ መሪ የጊዜውን አንገብጋቢነት ትልቅ ትኩረት ሰጥተዉበት አቋማቸዉን እንዲያስተካክሉ በአክብሮት እጠይቃቸዋለሁ። (አስተካክለውም ከሆነ እሰየው)

ኢትዮጵያዉያን በዚህ ጉዳይ ላይ ድምጻችንን ማሰማት አለብን። የህዝቡን ጥያቄ ሰምተዉም አመራር አባላቱ ዝምታን ከመረጡ፣ የነዚህ ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች አመራሮቻቸዉን ተጠያቂ ሊያደርጓቸው ይገባል። ከፊታችን እሁድ ጀምሮ ሰልፎች በጋራ ነው መደረግ አለባቸው ባይ ነኝ። ያ ካልሆነ አልሳተፍም ባሉት ድርጅቶች ላይ ተቃውሞ ማሰማት አለብን። ወያኔ የሕዝብን ጥያቄ እንደማያከበረው፣ እነርሱም የሕዝብን ጥያቄ ለስልጣን ወይም ድርጅት ፍቅር ሲሉ እያጣጣሉ ነው ማለት ነው።